# መግለጫ

## ሕዝቡን ያልወከለ መንግሥት ባለበት ሀገር፤ እንኳን በሀገር ቤት፤ በስደትም ሕዝቡ የሚሰቃይበት ሀቅ በላያችን ላይ ተጭኗል።

ሰኞ፤ ሚያዝያ ፲፪ ቀን፤ ፳፻፯ ዓመተ ምህረት

እኛ በሳን ሆዜና ሳን ፍራንሲስኮ ባህረ ሰላጤ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን፤ በሀገራችን ሆነ በስደት የሚንገላታውና ሕይወቱን የሚያጣው ወገናችን ስቃይ፤ ሰላም ነፍጎናል። ሰዎች በሀገራቸው ሰላም ሲያጡ፤ ሠርቶ መኖር ሲቸግራቸው፤ ማንነታቸው ለኑሮ ስቃይ ሲዳርጋቸው፤ ከዘመድ ተነጥለው፤ ሀገራቸውን ለቀው ለመሰደድ ይገደዳሉ። ይህ ነው አሁን የብዙዎች ኢትዮጵያዊያን ዕጣ። የሀገር ቤቱ የእስር ኑሮ አልበቃ ብሎ፤ በተሰደዱበት ቦታና ለመሰደድ በሚያደርጉት ጥረት ያጋጠማቸው ሀቅ፤ አረመኔያዊና አውሬያዊ ሆኖባቸው፣ በእሳት መቃጠላቸውን፤ በቦምብ መደብደባቸውን፣ በካራ መዘልዘላቸውንና በጎራዴ ራሳቸው መፈለጡን፤ በዓለም የዜና ማሰራጫ አውታሮች፤ ከዓለም ሕዝብ ጋር ተመለከትን። ሐዘናችን መጨበጫ ባጣ መንገድ ሰቀጠጠን። ባንድነት ሆነን ሐዘናችን መወጣቱ፤ ግድ አስተባበረን።

ኢትዮጵያዊያን በሳዑዲ አረቢያና በመካከለኛው ምሥራቅ የአረብ ሀገሮች የደረሰባቸው ግፍ ገና በልባችን ተደርድሮ መቀመጡን ሳያረጋግጥ፣ በደቡብ አፍሪቃ የደረሰባቸው በጎማ ታጉሮ በእሳት መጋየት፣ የመን በሳዑዲ አረቢያ የአየር ቦምብ መደምሰስ፣ በአይሲስ አረመኔ ጋጠ ወጦች አንገታቸው መቀላቱና በጥይት መደብደባቸው፣ በሜዲትራኒያን ባህር መስመጣቸው፤ ኢትዮጵያዊያንን በያለንበት አጥንታችን ሰብሮ የገባ ሐዘን ለቆብናል። በርግጥ ለዚህ ሁሉ ምንጭ አለው። አንደኛው ከሌላው ቢከፋና የበለጠ ቢሰቀጥጥም፤ በድምሩና በመሠረቱ፤ በሀገራችን ያለው የአስተዳደር ክፍል ዋና ተጠያቂ ለመሆኑ፤ ጥርጥር የለንም። ሰው ቢሰደድም ኢትዮጵያዊነቱ በኖ አይጠፋም። ኢትዮጵያዊያን በያለንበት የሚቆምልን መንግሥት የለንም።

ከሀገር ውጪ ያለን ኢትዮጵያዊያን፤ በያለንበት ስደተኞች ነን። ለኢትዮጵያዊያን፤ ከሀገራችን መሰደዱ፤ በሀገር ከመኖሩ የተሻለ አማራጭ እየሆነ የመጣበት ሀቅ፤ በላያችን ላይ ነግሷል። ለዚህ ነው ወገናችን የባህር ወለል ንጣፍ፣ የአረመኔ ማረጃያ ስለት ማቅለሚያ፣ የነበልባል እሳት ችቦ እየሆኑ ያሉት። ወላጆቻቸውና ዘመድ አዝማዳቸው በምን ያህል አንጀት የሚያራቁትና ሰውነት የሚያኮራምት ሐዘን ላይ እንደሆኑ እያሰብን፤ ፈጣሪያቸው ሐዘናቸውን ያቅልልላቸው፤ በልባቸው በትዝታ የያዙት ማስታወሻ መጽናኛ ይሁንላቸው እንላለን። እኛም ጥልቅ ሐዘን ተሰምቶናል። ይህ ጉዳይ ኢትዮጵያዊነታችን ከመሠረቱ ጠይቆታል። በአንድነት ሆነን፤ **"ይህ መቀጠል የለበትም!"** ማለት አለብን። ሀገራዊ ስደት ሆኖብናል። ሀገራዊ ሐዘን ሆኖብናል። ሀገራዊ ለቅሶ ሆኖብናል። እስከመቼ!

ሐሙስ፤ ሚያዝያ ፲፭ ቀን፤ ፳፻፯ ዓመተ ምህረት፤ ሳን ሆዜ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ግቢ፤ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን፤ ለሐዘን መግለጫ ሻማ ተሰብስበን አብርተናል። የከተማዋ ከንቲባና ካውንስል አባላት (Mayor and City Council Members) በአካል፣ አፍሪካ አሜራካዊ ማኅበራት (Local African American Associations) ተወካዮቻቸውን በመላክ፤ የ(National Association for the Advancement of Colored People – NAACP) ኤን ኤ ኤ ሲ ፒ ተወካይ ተገኝተው፤ የሳን ሆዜና ሳን ፍራንሲስኮ ባህረ ሰላጤ የጂዊሽ ተወካይ ( Representative of Jewish Community Centers of The Greater Bay Area ) ተገኝተው፤ በማኅበራቸው ስም የሐዘናችን ተካፋይ ሆነዋል። ዓለም አብሮን ቆሟል።

ይህ በደል፤ የኢትዮጵያዊያን መንግሥት በሀገራችን እስካልቆመ ድረስ፤ በከፋ ሁኔታ ይቀጥላል። ኢትዮጵያዊያን በያለንበት የዚህ ሐዘን ክብደት አስተባብሮን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ችግሩን ከሥሩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነቅሎ ለማጥፋት እያደረገ ላለው ትግል፤ በትብብር መቆም አለብን እንላለን። ኢትዮጵያዊ ግዴታ እንዳለብን መገንዘብ አለብን። ዛሬ ካሆነ መቼ! እኛ ካልሆን ማን! ብለን መጠየቅ አለብን።

**በሳን ሆዜና ሳን ፍራንሲስኮ አካባቢ የምንገኝ የወገን ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያን**